ሐምሌ 2012 ዓ.ም
July, 2020

# አዋሽ ዜና መጽሔት
# Awash Newsletter

በማርኬቲንግና ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚታተም

**Published by: Marketing & Communication Directorate**

8980
contactcenter@awashbank.com
www.awashbank.com

# በዚህ ዕትም


የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ስርጭት እና ተፅዕኖዎች ........ 1
የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመከላከል አዋሽ ባንክ የተለየዩ እርምጃዎችን ወሰደ ........ 2
አዋሽ ባንክ የኮሮና ቫይረስ ተጽዕኖን ያገናዘበ የወለድ ምጣኔ ቅነሳ አደረገ ........ 3
አዋሽ ባንክ ለብሔራዊ የኮቪድ-19 የድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴ
የብር 10 ሚሊዮን ድጋፍ አደረገ ........ 4
አዋሽ ባንክ በወረርሽኙ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እርዳታ አደረገ ........ 5
አዋሽ ባንክ እና ኢቢሲ የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረሙ ........ 6
የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመከላከል ........ 14
ኮሮና ........ 15


# In This Issue


**Awash Bank to construct new building** ........ 8
**Articles** ........ 9
**Quotes** ........ 12
**Photo Reel** ........ 17






# የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ስርጭት ሕና ተፅዕኖዎች

የመጀመሪያው የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ተጠቂ በሀገረ ቻይና በሁዋን ከተማ መታየቱ ሪፖርት የተደረገው እ.ኤ.አ. በህዳር 2019 ነበር። ቫይረሱ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍበት መንገድ እና የሚዛመትበት ፍጥነትን መነሻ በማድረግ የዓለም ጤና ድርጅትም ቫይረሱን በወረርሽኝነት በመፈረጅ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ ውሳኔ አስተላልፏል።

የኮሮና ቫይረስ በዓለማችን ላይ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ መተኪያ የሌለውን የሰው ልጅ ህይወት ከመቅጠፍም አልፎ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድቀትን እና ማህበራዊ ቀውስን እያስከተለ ይገኛል። የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች እንቅስቃሴዎችም ከመቀዛቀዛቸው የተነሳ በዓለማችን ላይ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችም ለስራ አጥነት ተዳርገዋል።

በአገራችን ደረጃም የቫይረሱን የስርጭት አድማስ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አገራችንም ከአለም ነባራዊ ሁኔታ ውጭ እንደማትሆን አስቀድሞ በመረዳት አስፈላጊ የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። በተለይም በቫይረሱ የተጠቃው የመጀመሪያው ግለሰብ በአገራችን ከታየበት ዕለት ጀምሮ የኢፌዲሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የወረርሽኙን ስርጭት ለመከላከል መደረግ በሚገባቸው የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎች ዙሪያ በየጊዜው የተለያዩ መመሪያዎችን አስተላልፏል፤ በማስተላለፍ ላይም ይገኛል።

በአገር አቀፍ ደረጃ የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከል የሚደረገው ጥረት ውጤታማ ይሆን ዘንድ ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ተቋማት ድረስ በየደረጃው በቡድንና በተናጠል የሚደረጉ ጥረቶች ከፍተኛ ድርሻ ይኖራቸዋል ተብሎ ይታመናል።

አዋሽ ባንክም ማህበራዊ ኃላፊነት እንዳለበት ግንባር ቀደም ተቋም የወረርሽኙን ስርጭት ለመከላከል ወረርሽኙ በአገራችን ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ በመንግስት ለተደረገው አገራዊ ጥሪ ምላሽ ከመስጠት አንስቶ የደንበኞቹንና የሰራተኞቹን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ በርካታ ስራዎችን ሰርቷል፤ እየሰራም ነው። በተለይም የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከል ሊደረጉ የሚገባቸው የቅድመ ጥንቃቄ ተግባራትን በስራ ላይ ከማዋል አንፃር ለደንበኞችና ለሰራተኞቹ የእጅ መታጠቢያ ስፍራን በማዘጋጀት፣ በሁሉም ቅርንጫፎች ውስጥ የማህበራዊ ፈቀቅታን ተግባራዊ በማድረግና ለሰራተኞቹ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ እና የእጅ ማፅጃ ሳኒታይዘሮችን በማቅረብ አስፈላጊውን ሁሉ በማድረግ ላይ ይገኛል።

እነዚህን የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃዎችን አልፎ ወረርሽኙ የባንኩን መደበኛ ስራዎች ሊያስተጓጉል በሚችል ደረጃ ሊከሰት የሚችልበት ሁኔታ ቢፈጠር እንኳን ባንኩ ለችግሩ መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችለውን መመሪያ በማዘጋጀት በሁሉም ቀጠናዎች እና ቅርንጫፎቹ ተግባራዊ እንዲደረጉ አቅጣጫ አስቀምጧል። ይህንንም ስራ በባለቤትነት የሚቆጣጠሩ ኮሚቴዎችን በየደረጃው በማዋቀር ወደ ተግባራዊ ስራ አስገብቷል።

# የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመከላከል አዋሽ ባንክ የተለየዩ እርምጃዎችን ወሰደ

አዋሽ ባንክ በሀገራችን ከቅርብ ግዜ ወዲህ በወረርሽኝ ደረጃ ከተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ጋር ተያይዞ ሊያጋጥም የሚችለውን የተለያዩ የንግድ ሂደት መስተጓጎልን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም የውድ ደንበኞቹን ግዜያዊ ችግር ለመቅረፍ የሚከተሉትን የአገልግሎት ክፍያ ማሻሻያዎችን አድርጓል። በዚሁ መሰረት : -

1. ከውጪ አገር የተለያዩ ዓይነት ምርቶችንና ሸቀጦችን ወደ ሀገር ለሚያስገቡ ኢምፖርተሮች ወይንም የባንኩ ደንበኞች ቀደም ሲል ለኤልሲ ማራዘሚያ ይከፍሉ የነበረው የኮሚሽን ክፍያ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳ በማድረግ አገልግሎቱን ምቹ በሆነ ሁኔታ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ አመቻችቷል ።
2. የባንካችን ደንበኞች ከዚህ በፊት ብድር ከወሰዱ በኋላ በተቀመጠው የግዜ ገደብ ውስጥ ሳይከፍሉ ቀርተው የብድር መመለሻ ጊዜው እንዲራዘምላቸው ለሚያቀርቡት ጥያቄ ይከፈል የነበረው የአገልግሎት ክፍያ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳ ተደርጓል ።
3. ደንበኞች ከኤቲኤም ማሽን ጥሬ ገንዘብ ሲያወጡ ከሂሳባቸው ላይ ይቆረጥ የነበረውን የአገልግሎት ክፍያ ሙሉ በሙሉ እንዲቀር ተደርጓል ።

በአለም ጤና ድርጅት በወረርሽኝነት የተፈረጀው የኮሮና ቫይረስ በዓለማችን ላይ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ መተኪያ የሌለውን የሰው ልጅ ህይወት ከመቅጠፍም አልፎ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድቀትን አስከትሏል። የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች እንቅስቃሴዎችም ከመቀዛቀዛቸው የተነሳ በዓለማችን ላይ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችም ለስራ አጥነት ተዳርገዋል።

ባንካችንም ወረርሽኙን ለመግታት ግዜያዊ ኮሚቴዎችን በማዋቀርና በማደራጀት በርካታ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ሲሆን ከዋና መስሪያ ቤት እስከ ቅርንጫፎች የቅድመ ጥንቃቄ ስራውን ተግባራዊ በማድረግ በመግቢያ በሮች ላይ ለደንበኞቹና ለሠራተኞቹ የእጅ መታጠቢያ ቦታን በማዘጋጀት እጃቸውን በአግባቡ በሳሙና ታጥበው እንዲገቡ በማድረግ ላይ ይገኛል።



በዋ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ለደንበኖች የተዘጋጀ የእጅ መታጠብያ

ባንካችንም ወረርሽኙን ለመግታት ግዜያዊ ኮሚቴዎችን በማዋቀርና በማደራጀት በርካታ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ሲሆን ከዋና መስሪያ ቤት እስከ ቅርንጫፎች የቅድመ ጥንቃቄ ስራውን ተግባራዊ በማድረግ በመግቢያ በሮች ላይ ለደንበኞቹና ለሠራተኞቹ የእጅ መታጠቢያ ቦታን በማዘጋጀት እጃቸውን በአግባቡ በሳሙና ታጥበው እንዲገቡ በማድረግ እንዲሁም ከአላስፈላጊ መጠጋጋቶችና ከመጨባበጥ በመታቀብ የቫይረሱን ስርጭት በመግታት ዙሪያ ሁሉም ሠራተኛ የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ላይ ይገኛል።

ከዚህም በተጨማሪ ሠራተኞች ወደ ውስጥ ከገቡ በኋላ በስራ ምክንያት ከተለያዩ የቢሮ ዕቃዎች ንኪኪ ጋር በተያያዘም የእጅ ማፅጃ ሳኒታይዘር በየቢሮ እያቀረበላቸው ሲሆን ካውንተሮችን፣ የበር እጀታዎችና አሳንሰሮችም በየሰዓቱ እንዲፀዱ በማድረግ የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከል አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ላይ ይገኛል።

# አዋሽ ባንክ የኮሮና ቫይረስ ተጽዕኖን ያገናዘበ የወለድ ምጣኔ ቅነሳ አደረገ

የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኙ በአገራችን መከሰቱን የኢፌዴሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ካሳወቁበት ጊዜ አንስቶ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ እየተስተዋሉ ያሉ ተፅእኖዎች ቀላል የሚባሉ አይደሉም፡፡ ይህ ወረርሽኝ በንግድ እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረውን ተፅእና ከግምት ውስጥ በማስገባት አዋሽ ባንክ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የተለያዩ ማሻሻያዎችን አድርጓል፡፡

የወለድ ምጣኔ ቅነሳው የተደረገላቸው የኢኮኖሚ ዘርፎችም የሆቴል እና ቱሪዝም፣ የጉዞና አስጎብኚ ድርጅቶች እና የአበባ አምራች ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡

በዚሁ መሰረት ቀደም ሲል ይከፍሉ ከነበረው ምጣኔ ለሶስት ወራት ወደ ዝቅተኛው የወለድ ምጣኔ ማለትም ወደ (7%) ሰባት በመቶ እንዲቀንስላቸው ተደርጓል፡፡ ባንኩ ይህንን የወለድ ቅነሳ በማድረጉም በትንሹ እስከ ብር 50 ሚሊዮን የሚደርስ ገቢ እንደሚያጣ ተገምቷል፡፡




የአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ፀሀይ ሽፈራው የወለድ ምጣኔ ቅነሳ አስመልክተው መግለጫ በሰጡበት ወቅት

# አዋሽ ባንክ ለብሔራዊ የኮቪድ-19 ድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴ የብር 10 ሚሊዮን ድጋፍ አደረገ

አዋሽ ባንክ የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመግታት የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ የብር አስር ሚሊየን ድጋፍ ለብሔራዊው የኮቪድ-19 የድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴ አስረክቧል፡፡

የኮሮና ቫይረስ በሀገራችን በወረርሽን ደረጃ በመከሰቱ ሊያስከትላቸው የሚችለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በመንግስት ደረጃ የቅድመ መከላከል ስራዎችን ከማከናወን በተጨማሪ በርካታ የጥንቃቄ እርምጃዎችና ውሳኔዎችን በማስተላለፍ እንዲሁም ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት የእርዳታ ድጋፍ ጥሪ መደረጉ የሚታወቅ ነው፡፡

አዋሽ ባንክም ከምስረታው ጀምሮ የፋይንናንስ አገልግሎት ለውድ ደንበኞቹ ከመስጠቱ ጎን ለጎን ቀደም ሲል ለበርካታ ዓመታት በሃገሪቱ ለሚከሰቱ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ ተግዳሮቶችን ለመመከት የሚያስችሉ የፍይናንስ እገዛ በማድረግ ማህበራዊ ሀላፊነቱን በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡

ዘንድሮም በሰላም ሚኒስቴር ለሚመራው ለብሔራዊው የኮቪድ-19 የድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴ በባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ክቡር አምባሳደር ዶ/ር ዲባባ አብደታ አማካኝነት የብር አስር ሚሊየን የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል፡፡ አምባሳደር ዶ/ር ዲባባ አብደታ በድጋፍ ማሰባሰብያ ሥነ-ሥርዓቱ ወቅት እንደተናገሩት በዚህ አስቸጋሪ ግዜ የተለመደውን የኢትዮጵያዊነትና የመረዳዳት መንፈስ በማጎልበት አንድነታችንን በይበልጥ ማሳየት እንደሚገባ ጠቅሰው ባንኩ በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ከምንግዜውም በላይ ከመንግስት ጎን መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ብሄራዊ የድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚያካሂደው የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን የመከላከል ዘመቻ ገንዘብ ለማሰባሰብ በአዋሽ ባንክ የከፈተው የሂሳብ ቁጥር 01304794745400 መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡




ክቡር አምባሳደር ዶ/ር ዲባባ አብደታ በሥነ-ሥርዓቱ ወቅት የብር 10 ሚሊዮን ቼክ ለድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴ ሲያስረክቡ

# አዋሽ ባንክ በወረርሽኙ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እርዳታ አደረገ

የኮሮና ቫይረስ ወደ አገራችን መግባቱን የኢፌዲሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ማሳወቃቸውን ተከትሎ በአገራችን በተፈጠረው የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ምክንያት በርካታ ወገኖቻችን ለኢኮኖሚያዊ ችግሮች እየተጋለጡ ነው። ቫይረሱ በህብረተሱ ጤና እና ገቢ ላይ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተፅእኖ ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ መንግስትም የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል። አዋሽ ባንክም የመንግስትን እርምጃ በመደገፍ ቀደም ሲል ለአገር አቀፍ እርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ የአስር ሚሊዮን ብር ድጋፍ ያበረከተ ሲሆን፣ የሚያግዟቸው ደጋፊ ወላጆች ለሌላቸው ተማሪዎች የመመገቢያ ድጋፍ ይሆን ዘንድም በፋሚሊ መርሲ ሀውስ በኩል የአንድ መቶ ሺህ ብር እርዳታ አድርጓል።

በሌላ በኩል ከበድር ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ በወረዳ 06 በኮሮና ቫይረስ ምክንያት ለችግር ለተጋለጡ ህብረተሰብ ክፍሎች የብር 500 ሺህ ልገሳ አድርጓል። ይህ የተለገሰው ገንዘብም ለ250 አባወራዎች ለአንድ ወር ቀለብ መግዣ እንደሚውል ፋውንዴሽኑ አስታውቋል።

በስፍራው በመገኘት ለተረጂዎች ዕርዳታውን የሰጡት የአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ፀሀይ ሽፈራው ባደረጉት ንግግር አብሮን በኖረው የመደጋገፍ አኩሪ ኢትዮጵያዊ ባህላችን ይህንንም ጊዜ እናልፋልን የሚል ፅኑ እምነት እንዳላቸው ገልጸው ይህንን ችግር እስከምንሻገር ድረስ ባንኩ የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑንም አስረድተዋል።




አቶ ፀሀይ ሽፈራው በሥነ - ሥርዓቱ ወቅት የቼክ ስጦታ ሲያበረክቱ

# አዋሽ ባንክ እና ኢ.ቢ.ሲ የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረሙ




በመግባብያ ስምምነቱ ወቅት የተደረገ ሥነ - ሥርዓት

አዋሽ ባንክ እና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በቀጣይ ጊዜያት በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረሙ፡፡

የመግባብያ ስምምነቱ ዋና አላማ የደንበኞቹን ፍላጎት ለማርካትና ዘመኑን የዋጁ ቀልጣፋ የባንክ አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ በመስጠት ላይ የሚገኘው አዋሽ ባንክ አዳዲስ የባንኪንግ ቴክኖሎጂዎችን በሃገሪቱ አንጋፋ እና በስርጭት ሽፋኑ ግንባር ቀደም የመንግስት የሚዲያ ተቋም ከሆነው ኢ.ቢ.ሲ ጋር በጋራ በመስራት በሰፊው ለማስተዋወቅና እየሰጠ በሚገኘው የባንኪንግ አገልግሎቶች ላይ በቂ ግንዛቤ ለመፍጠር ነው፡፡ በመሆኑም የመግባቢያ ስምምነቱ ለሁለቱ ተቋማት ለአገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጥ አብረውና ተደጋግፈው ለመስራት ምቹ መደላድልን የሚፈጥር ነው፡፡

የመግባቢያ ስምምነቱ የተፈረመው በአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈፃሚ በአቶ ፀሐይ ሽፈራው እና በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ በዶ/ር ንጉሴ ምትኩ ታህሳስ 19 ቀን 2012 ዓ.ም በረመዳ ሆቴል ነበር::

ከዚህም በተጨማሪ ስምምነቱ የባንኩ አገልግሎቶች በየጊዜው ለህብረተሰቡ እንዲደርሱና ህብረተሰቡም የአገልግሎቶቹ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡ እንደዚሁም ኢ.ቢ.ሲ አገልግሎቱን ለማዘመንና ተደራሽነቱን ለማስፋፋት የሚያደርገውን ጥረት ባንኩ በሚችለው አቅም ሁሉ እንደሚያግዘው ተጠቁሟል፡፡

# ikhlas




## የተሟላ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

# Awash Bank to construct new building



Awash Bank signed contractual agreement with Tilahun Abebe General Contractor for the construction of Bale Robe branch office.

The building will have 4 floors with a project completion time of 540 calendar days. The contractual agreement has been signed by Ato Tsehay Shiferaw, Awash Bank's Chief Executive Officer and Ato Tilahun Abebe Managing Director of the Construction Company.

The managing Director confirmed that, as the Construction Company is well experienced in the industry, it works hard to meet the contract management principle in all aspects.

# WHO statement: Tobacco use and COVID-19

Tobacco kills more than 8 million people globally every year. More than 7 million of these deaths are from direct tobacco use and around 1.2 million are due to non-smokers being exposed to second-hand smoke.

Tobacco smoking is a known risk factor for many respiratory infections and increases the severity of respiratory diseases. A review of studies by public health experts convened by WHO on 29 April 2020 found that smokers are more likely to develop severe disease with COVID-19, compared to non-smokers.

COVID-19 is an infectious disease that primarily attacks the lungs. Smoking impairs lung function making it harder for the body to fight off corona viruses and other diseases. Tobacco is also a major risk factor for no communicable diseases like cardiovascular disease, cancer, respiratory disease and diabetes which put people with these conditions at higher risk for developing severe illness when affected by COVID-19.

Available research suggests that smokers are at higher risk of developing severe disease and death.

WHO is constantly evaluating new research, including research that examines the link between tobacco use, nicotine use, and COVID-19.

WHO urges researchers, scientists and the media to be cautious about amplifying unproven claims that tobacco or nicotine could reduce the risk of COVID-19. There is currently insufficient information to confirm any link between tobacco or nicotine in the prevention or treatment of COVID-19.

Nicotine replacement therapies, such as gum and patches are designed to help smokers quit tobacco. WHO recommends that smokers take immediate steps to quit by using proven methods such as toll-free quit lines, mobile text-messaging programmed, and nicotine replacement therapies.

Within 20 minutes of quitting, elevated heart rate and blood pressure drop. After 12 hours, the carbon monoxide level in the bloodstream drops to normal. Within 2-12 weeks, circulation improves and lung function increases. After 1-9 months, coughing and shortness of breath decrease.

Source:- www.who.int/COVID-19

# Can Ethiopia banking Sector help to mitigate the Economic impact of COVID-19?

With the outbreak of COVID-19, we are observing unprecedented economic changes and Ethiopia is trying to adapt to a new normal. The economy is suffering and sectors like tourism and hospitality are witnessing their worst days. The financial sector in general and the banking sector, in particular, are no exception. However, besides working to resolve its own liquidity issues, is the sector adapting quickly enough and playing its part to help businesses and the economy?

The financial sector plays an important role in the economy through the mobilization of savings from depositors and disbursing that money to businesses in the form of loans. This channeling of resources to businesses is the backbone of the economy and a huge source of local funding for businesses. Tasked with the same responsibility, the Ethiopian financial sector has been recording significant year-over-year growth. According to the National Bank of Ethiopia's (NBEs) 2018/19 Annual Report, deposit liabilities of the banking system topped ETB 899.6B and the total outstanding borrowing stoodat ETB 164.5B.
Considering the role of the banking sector in the national economy, the NBE has availed ETB 15 B for the banking sector as Ethiopia reported the first case of COVID-19 on March 13. Simultaneously, NBE has released part of the Great Renaissance Dam Bill Bond that commercial banks have purchased.

Nevertheless, by some standards, NBE has been slow to introduce new monetary policy changes that could help fight the impact of COVID-19 on businesses and the economy as a whole. As a governing body of the financial sector, NBE has the obligation and resources to take proactive measures to help flatten the impact of COVID-19 on the economy.

NBE can take three vital measures that could help commercial banks deal with the challenges that COVID-19 brought:

- Lower the savings interest rate
- Release part of the legal reserve to commercial banks
- Release part of the liquidity reserve to commercial banks

Lower the savings interest rate – NBE last made changes to the savings interest rate in October 2017 pushing it to 7% from 5%. The average lending rate of the banking sector was 13.5% for the 2018/19 fiscal year. Since then, some banks have made changes to the lending interest rates by lowering rates ranging from 0.5% to 5%. Regardless, the industry-wide average lending rate remains high for a challenging time such as this. As such, NBE should intervene and lower the savings interest rate to help commercial banks lower their lending interest rates. Lower

Continued to the next page.....

interest rates will mean cheaper loans for businesses and households. That will reduce the costs faced by businesses and households in Ethiopia.

Release part of the legal reserve to commercial banks – Commercial banks in Ethiopia are obliged to set aside 25% of their net profit annually and, currently, each commercial bank has set aside funds accumulated over several years as there have not been incidents forcing the release of these funds. This legal reserve is set aside as a shock absorber to help protect the shareholders and the public interest. The current situation, if not dealt with early, could cause a long-term economic disruption and result in a number of job losses. NBE could release part of the funds to commercial banks in different tranches and set guidelines to help coordinate efforts and avail funds at a lower interest rate to hard-hit sectors such as tourism, hospitality, manufacturing and micro, small and medium enterprises (MSME), sectors that create a large number of jobs in the economy.

Release part of the liquidity reserve to commercial banks – Commercial banks are also obliged to set aside at least 15% of their net current liabilities to help protect depositors against economic shocks.

This could be another source of funding for commercial banks. If NBE allows banks to use part of the reserve by setting the same guidelines as the legal reserve and supervising banks to make sure they disburse the loan to priority sectors at a lower interest rate, it could be a savior for many businesses and the economy in general.

In addition to the monetary policy changes suggested above, commercial banks (both private and public) should also work internally to help the economy bounce back. Thus far, commercial banks have taken some initiatives to that end. These include giving donations to the government, waiving some of the service charges, and lowering the interest rate for certain sectors. Though these are good efforts, believe that these efforts are far behind what businesses and the economy need. This is the time for the executive management and board of directors of each bank to work together and come up with creative solutions. To mention a few, banks should consider suspending payment of accrued dividends and also hold on to future distributions until the economy stabilizes.

We are in a time of uncertainty. The effect of COVID-19 is not only taking lives but also disrupting the economy. Thus, it requires the coordinated efforts of both the public and the private players. People and organizations should work hand-in-hand to help mitigate the effects of COVID-19.

It is important to be proactive and take measures before things get any worse. The banking sector, as the nucleus of the economy, should present itself as the forerunner in these efforts and continue to push for alternative banking solutions to help the economy recover faster from this crisis. As the regulator and the captain of the banking sector, NBE plays a pivotal role in all of these efforts. Commercial banks, both public and private, should also help and push NBE to make smart and sound monetary policy changes to help equip them

with the resources and policy frameworks to fight the economic impact of COVID-19.

Impacts of Corona Virus on Banks

Banks Already facing very tight liquidity conditions even before the corona crisis (most private banks have effective loan-to-deposit ratios near/above 100%), banks are now threatened by a potential jump in NPLs as businesses become unable to service loan repayments.

While Birr 15bn of liquidity support has recently been announced for the sector, bankers have been underwhelmed by this offer and found it largely inadequate. As relayed by those in the sector, the Birr 15bn has been offered against the stock of NBE Bill repayments that Banks were to receive from NBE in the coming year up to June 2021; effectively, the NBE is buying back these Bills and providing banks upfront liquidity in exchange (similar to central bank bond-buying programs in countries with open market operations). However, we understand that deductions are applied to amounts the banks may have still owed to NBE when the policy was discontinued back in November 2019, and so the overall liquidity injection for banks is less than the headline figure may suggest. Moreover, as banks already had outstanding short-term loans due to NBE from recent borrowings (which added up to Birr 14.5bn from emergency loans given out in January and February 2020), most of the fresh funds made available as part of the corona response may effectively be absorbed by those repayments, leaving banks and hence their customers with much fewer net resources.

(Source-renew@renewstrategy.com)

## Quotes

The wise man does not expose himself needlessly to danger, since there are few things for which he cares sufficiently; but he is willing, in great crises, to give even his life - knowing that under certain conditions it is not worthwhile to live.

-Aristotle-

“It’s not how much money you make, but how much money you keep, how hard it works for you, and how many generations you keep it for.”

—Robert Kiyosaki-

# ኮሮና ቫይረስን በጋራ እንከላከል!!

## የበሽታው ምልክቶች | Symptoms




ትኩሳት
**High Fever**



የትንፋሽ ማጠር
**Trouble Breathing**



ሳል
**Cough**

## የሚደረጉ ጥንቃቄዎች | Prevention



አለመጨባበጥ
do not shake hands



ባልታጠበ እጅ ፊትዎን አለመንካት
Avoid touching Eyes, Nose & Mouth



አፍን መሸፈን
Use face mask



እጅ በሳሙና መታጠብ
Wash your hands with soap & water



አካላዊ ርቀትን በ2 ሜትር መጠበቅ
Keep 2m distance from others

# የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመከላከል ፡ -

- እጅን በንጹህ ውሃና ሳሙና አዘውትሮ መታጠብ እና  አለመጨባበጥ፣
- አካላዊ ርቀትን በመጠበቅ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖርን አላስፈላጊ ንክኪን ማስወገድ፣
- ሳል ወይም ትኩሳት ካለው ግለሰብ ቢያንስ ሁለት እርምጃ ርቀት ያህል መራቅ፣
- አይንና አፍንጫን እጅን ሳይታጠብ አለመንካት፣
- በሚያነጥሱበት እና በሚያስሉበት ጊዜ አፍና አፍንጫን በሶፍት ወይም ክርንን አጥፈው በመጠቀም ወደ ሌሎች እንዳያስተላልፉ መጠንቀቅ፣
- የተጠቀሙበትን ሶፍትና ተመሳሳይ ነገሮች በቆሻሻ ክዳን ባላቸው ማጠራቀሚያ ማስወገድ፣
- በስራ ቦታ፣ በትራንስፖርት እና መኖሪያ ወይም የመኝታ ክፍል መስኮት በመክፈት በቂ አየር እንዲኖር ማድረግ፣
- በተለይ በባንካችን ቅርንጫፎች ውስጥ መጨናነቅን ለመቀነስ የሞባይል ባንኪንግ ኢንተርኔት ባንኪንግ የኤቲኤም እና የግብይት ማሽን አገልግሎት መጠቀም በዋነኝነት ይገኙበታል፡፡

## “ኮሮና”

ከሩቅ ምስራቅ ማዶ ከአድማስ ባሻገር፣
መነሻውን አርጎ በቻይኖች ሀገር፣
ዘር ቀለምን ሳይለይ ሁሉን ሲያደናግር፣
ስንቱን ቀላቀለ ከመሬት ከአፈር።
የአለም ሳይንቲስቶች መፍትሄው ጠፍቷቸው፣
ሊቅ ጠቢባኖቹ  እድል ሳይቀናቸው፣
ቀን በቀን ቫይረሱ እየተዛመተ፣
መላው የሰው ልጅን ከእቤት ውስጥ ከተተ።
ድምፅ አልባው ወረርሽኝ መቸ በዚህ አበቃ፣
የሀዘን ማቅ አልብሶ ሲያመጣ ሰቆቃ፣
ከቶ መች ታወቀ የሁሉም ፈረቃ፣
እረ ጎበዝ ወገን በግዜ እንንቃ።
የታል ጥንቃቄው ሲነገር በምላስ፣
እያዩ አለማያት ጆሮ ዳባ ልበስ፣
ሩጫና ጥድፊያው ከቶ የትስ ሊያደርስ፣
የስጋዊ ምቾት መች ጠቀመ ለነብስ።
ይልቅ እንጠንቀቅ የሚባለውን እንስማ
ከሌላው እንማር አንሁን ደካማ
ጸጸቱ ሳይውጠን የሀዘን ጨለማ
ዛሬ ልብ ይኑረን ለያዝነው አላማ : :

(ሰላም ተክለጽዮን
ማርኬቲንግና ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
አዋሽ ባንክ)

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like The River

# Use your cards




MasterCard VISA UnionPay 银联

@
**Awash ATMs and POS terminals!**

*We are determined to simplify your way of doing business!*

# . . . ህልምዎን ዘርተዉ ያብቅሉ!




አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River